የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
**UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)**

## የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) በዩትሬክት ሆላንድ ላይ ከተፈጠረው "ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ (አልያንስ)" ጋር ስላለው ልዩነት የተሰጠ መግለጫ

### ራእያችን - ስጋታችን፤

ዛሬ በአገራችን ያለው ሁኔታ ሕዝባችን ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ የተቃዋሚ ኃይሎችን የትግል አንድነት የሚጠይቅበት ወቅት ነው:: በዚህ ሁኔታ ኢዴኃኅ (ኅብረት) በቅርቡ ዩትሬክት÷ ሆላንድ ላይ በተፈጠረው 'ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ' ውስጥ አባል አይደለሁም÷ አልሳተፍበትም ማለቱና በዚህ ዙሪያ አቋሙን ማሳወቁ ብዙ ዴሞክራትና አገር-ወዳድ ወገኖችን ግራ ሊያጋባ እንደሚችል ይሰማናል::

የስብሰባው አዘገጃጀትና አጠራር የፖለቲካ ድርጅቶች በአገር እና በሕዝብ ጉዳይ ለመምከር መከተል ካለባቸው መደበኛ የስብሰባ አጠራር አካሄድ ውጭ እንደሆነ ግልጽ ነው:: ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል ባወጣናቸው ጽሑፎች እንደተጠቀሰው ሁሉ ይኸ ስብሰባ እንዴትና ከነማን ጋር በምክክር መጠራት እንደሚኖርበት በተለይ ከኦነግ ጋር ውይይቶች እየተደረጉና መሠረታዊ መግባባቶች ላይ እያለን በዚህ ስብሰባ ላይ እንድንገኝ ጥሪው ድንገት ሲደርሰን በአስማነው የአግራሞት ተቃውሞ በቃልም በጽሑፍም የተረጋገጠልን ስብሰባው የመጀመሪያ ደረጃ (preliminary) ስብሰባ እንደሚሆንና የመወያያ አጀንዳውም እዛው በተሰብሳቢው የሚወሰን እንደነበር ነው:: ሆኖም ኅብረቱ ጥሪውን አክብሮና ቃሉን ጠብቆ ተወካዮቹን በተባለው የስብሰባ ቦታ እንዲገኙ ሲያደርግ የገጠመው ያልጠበቀው ሁኔታ ነበር:: የስብሰባው አጀንዳ በተወሰኑ ተሳታፊዎች አስቀድሞ ተወስኖ÷ ሰነድ ተዘጋጅቶ÷ በፊርማ አጽድቆ ለመለያየት ፍጥምጥሙ ያለቀበት ሁኔታ ነው የተከሰተው:: እንደሚታወቀው እኛም አስቀድሞ በተደረጉ ውይይቶች እንዳስረዳነውና መግባባት አለ ብለን የተማመንበት÷ እንደዚህ ዓይነት በአገርና በሕዝብ ጉዳይ ላይ ለመምከር የሚደረግ ስብሰባ ሰነድ በጋራ ተዘጋጅቶ÷ ለየተሳታፊ ድርጅቶች አስቀድሞ ተላልፎ÷ ድርጅቶቹ ከአባሎቻቸው ጋር የሰከነ ዴሞክራሲያዊ ውይይት አድርገውበት÷ የሚጨምሩትን ጨምረው÷ የሚቀንሱትን ቀንሰው÷ አስፈላጊም ሲሆን ተለዋጭ ሰነድ አሰናድተው ለአዘጋጁ ክፍል አቅርበው÷ አዘጋጁ ክፍል በሁሉም ከቀረቡት ሰነዶች የተቀናበረ÷ የማያግባቡ ነጥቦችም ካሉ እነሱም ተለይተው በስብሰባው ላይ በውይይት እንዲፈቱ አንድ የጋራ ሰነድ ይዞ መቅረብ በተገባ ነበር:: በዚህ ስብሰባ ላይ የተደረገው ይኸ አልነበረም:: የ'ትብብሩ (አልያንሱ)' ፕሮግራምና ደንብ ቀደም ብሎ ታድሎ በየድርጅቶቹ ዴሞክራሲያዊ ውይይት ተካሂዶበት ሃሳብ ይዞ ለመምጣት የሚቻልበት ሁኔታ አልነበረም:: የተጠቀሱት ሰነዶች ቅዳሜ ዕለት ጧት እዛው ስብሰባ አዳራሽ ላይ ለተሰብሳቢው ታድለው "አንብቧቸውና በአንድ ሰዓት ተኩል ውስጥ ስብሰባ ይጀመራል" ተባለ:: በዚያች አንድ ሰዓት ተኩል ውስጥ እንኳን ለአቋማችን የበሰለ መከራከሪያ ማቅረብ ይቅርና በጣም ዓይን ከሚያወጡት ይዘቶች በስተቀር ሰነዶቹ ሊይዟቸው የሚችሉትን ግድፈቶች በሙሉ ማየት የሚቻልበት ሁኔታ አልነበረም:: የጋራ ትግልን ጉዳይ ለአገራችን የወደፊት እጣ ፈንታ ወሳኝ አድርገን በመቁጠራችን እነዚህን ሰነዶች ከሚሏቸው ብቻ ሳይሆን ከማይሏቸውና ከዘለሏቸው ነጥቦችም አንፃር በጥሞና መመዘን ያስፈልግ ነበር:: ነገር ግን ይታረሙ ከሚባሉት ነጥቦች በተጨማሪ ይጎድላሉ የተባሉትንም ነጥቦች በእርጋታ ጊዜ ወስዶ ለማየት አስፈላጊ የሆነው ፋታ አልተገኘም::

አሉባልታውን ወደጎን ብንተወው÷ የብዙ ቅን ወገኖቻችን ክርክር "ምንም ያኽል ልዩነት ቢኖርስ ለምን እዛው ውስጥ ሆነው ነገሮችን ለማስተካከል አይሞክሩም ነበር" የሚል

እንደሆነ ይገባናል:: እንደሚታወቀው ኅብረቱ በዚህ ስብሰባ ሲገኝ ቀደም ሲል ከተነገረውና ቃል ከተገባለት ውጭ ሆኖ ሲያገኘው ስብሰባውን ከጅምሩ ጥሎ በመውጣት ፋንታ በሃላፊነት ስሜት በስብሰባው ውስጥ ሆኖ የሚችለውን ያኽል ከስብሰባው አካሄድ እስከ ይዘቱ ድረስ የተንፀባረቁና የቀረቡ ነጥቦች ላይ በግልጽና በቅንንነት ተከራክሯል::

ስብሰባው አስቀድሞ የተወሰኑ ጉዳዮችን ለማጽደቅ የተቆረጠ እንደሆነና ከዚህ ውጭ ምንም ለውጥ ማምጣት አለመቻሉን ኅብረቱ ተገንዝቧል:: ይኽ ደግሞ ኅብረቱ ከሚታገልለት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን እምነትና ዓላማ፥ በውስጡ ከሚከተለው ዴሞክራሲያዊና በመግባባት ላይ የተመሠረተ አሠራር ጋር ተጣጥሞ አላገኘውም:: ያም ሆኖ ግን ኅብረቱ በዚህ ስብሰባ የሚቻለውንና የሚጠበቅበትን ሁሉ አድርጓል:: በመጨረሻም ለጋራ ትግሉ መልካምና ጠቃሚ የመሰለውን አሳብ ለስብሰባው ተሳታፊዎች በደብዳቤ በመግለጽ ነው ከስብሰባው የወጣው::

በዚህ ደብዳቤም ኅብረታችን የተቃዋሚ ኃይሎችን መሰባሰብ የሚፈልግ ብቻ ሳይሆን እየታገለበት ያለ ጉዳይ በመሆኑ፤

ሀ)- በዚህ ስብሰባ የተካፈሉ ሁሉ የጋራ ስብስብ (አልያንስ) ለመፍጠር በመሠረተ ሃሳብ ደረጃ እንዲስማሙና ይኽንንም በጋራ መግለጫ ይፋ እንዲያደርጉ፤

ለ)- የጋራ ስብስብ ለመፍጠር በተደረገው መሠረታዊ ስምምነት መሠረት ሌሎች ዴሞክራሲያዊና አገር-ወዳድ ኃይሎችን የጨመረና ሰፋ ያለ ጉባዔ የሚያዘጋጅ በስብሰባው ተካፋይ ከሆኑ ድርጅቶች የተውጣጣ አንድ ጉባዔ አዘጋጅና አስተባባሪ ግብረ-ኃይል (የቀውጢ ጊዜ ግብረ-ኃይል) እንዲቋቋምና ተግባሩና ሃላፊነቱ በዝርዝር እንዲሰጥ፤

ሐ)- ይኽ አዘጋጅ ግብረ-ኃይል ከአንድ ወር ወይም ወር ተኩል ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በተሰጠው ሃላፊነት መሠረት አስፈላጊ ሰነዶች ከአባላት በማጠናቀርና ሌሎች ዝግጅቶችን በማጠናቀቅ ሰፋ ያለ ጉባዔ እንዲጠራና የተቃዋሚው የጋራ ስብስብ (አልያንስ) በጠነከረ መሠረት ላይ ተመሥርቶ የሚጠበቅበትን የጋራ ትግል አቅጣጫ የማስያዝና የሕዝቡን ትግል ሕዝባችን የሚከፍለውን መስዋዕትነት በሚመጥን መልኩ ለፍሬ የማብቃት ታሪካዊ ተልእኮ እንዲወጣ ማስቻል፤

የሚሉ ፍሬ ሃሳቦችን በማቅረብ ነው ያለበትን ሃላፊነት ለመወጣት ጥረት ያደረገው::

የጋራ ትግልን ጉዳይ ከማንም በላይ ሲያራምድ የቆየ ብቻ ሳይሆን የተፈጠረበት ዓላማውም የሆነው ኅብረታችን "ነገሮች በሂደት ይስተካከላሉ" በሚል ተስፋ ብቻ እዚህ ስብስብ ውስጥ ዘው ብሎ ከመግባት ይልቅ መመሥረቻ ሰነዶቹ ላይ ፊርማውን ላለማስቀመጥ ሲወስን ከሚከተሉት ዋና ዋና ነጥቦች ተነስቶ ነው::

<u>አንደኛ፡- የስብሰባውን ይዘት በተመለከተ፤</u>

የስብሰባው ተሳታፊ የሆኑ የየድርጅቱ ልዑካን ለአንድ ሰዓት ተኩል አንብበው እንዲወያዩባቸው ከተሰጡ ሁለት ሰነዶች ተነስተን ስንመለከተው ለሕዝባችን ይጠቅማል ብሎ ኅብረታችን ካነገበው ራእይና በተለይም ደግሞ ይኽንን እውን ለማድረግ ያስፈልጋል ብሎ ከሚያምንበት የጋራ ትግል እስትራቴጂ አንፃር ከባድ የሆኑ መሠረታዊ ልዩነቶች እንዳሉ ተከስቷል:: እነዚህ ልዩነቶች መሠረታዊ በሆኑ የትግሉን፥ የሕዝባችንንና የአገራችንን እጣ ፈንታ በሚወስኑ ጥያቄዎች ላይ የጋራ ግንዛቤ ማጣት ላይ የተመሠረቱ ናቸው:: በእነዚህ መሠረታዊ ጥያቄዎች አምስቱ ድርጅቶች በአንድ በኩል ኅብረቱ በሌላ በኩል ቆመው በስብስቡ ውስጥ በተለይ ቀደም ሲል የጋራ ግንባር በመሠረቱ የብሔር ድርጅቶች ከወዲሁ የተበጀ አብላጫ (ማጆሪቲ) ባለበት ሁኔታ ነገሮችን "ከውስጥ ሆኖ ማስተካከል" የሚባለው አካሄድ የሚያዋጣና ትክክል ሆኖ አላገኘነውም:: የአቶ መለስን ሕወሓት በመአከላዊነት ይዞ የሽግግር መንግሥት የመሠረተው የሰኔ ፺፫ (91) የአዲስ አበባ ጉባዔ ይዞ የወጣውን መልክ ይዞ የወጣውና ከዚያ ጀምሮ ላለፉት አሥራ-አምስት ዓመታት አገራችንንና ሕዝባችንን እያመሰ የሚገኘው ሁኔታ የተመቻቸው ቀደም ሲል ለንደን ላይ

በተደረገው የተወሰኑ ድርጅቶች ብቻ በተሳተፉበት ዝግ ስብሰባ መሆኑ ከቶውንም ሊረሳ አይገባውም::

ሁለተኛ:- በተከሰቱት ልዩነቶች ላይ ሰፊ ውይይት ስለማካሄድ፤

ትግሉ የጋራ፥ የኃይሎች ስብስብም የሚታገልለት ጉዳይ በመሆኑ ኅብረቱ በዚህ 'ትብብር (አልያንስ)'ን በፈጠረ የዩትሬክት ስብሰባ ላይ በውስጡ ተሳታፊ ሆኖ፥ በኢሕአዴግ ሕገ-መንግሥትም ይሁን በቋንቋ ዙሪያ፥ በስያሜም ይሁን ሕዝባችን አይከፍሉ መስዋዕትነት የከፈለበትና እየከፈለበት ባለው በምርጫ ፺፯ ዙሪያ፥ ወዘተ... ከባድና ጊዜ በሚጠይቁ ውይይቶች ብቻ ሊፈቱ የሚችሉ ልዩነቶች እንደተከሰቱ ተገንዝቧል::
ኅብረቱ በዚህ ስብሰባ ላይ በነዚህና በሌሎች ብሔራዊና አገራዊ ጉዳዮች ላይ፥ ለጋራ ጥቅሞች የተሻለ የሚመስለውንና የሚያምንበትን በግልፅና በቅንነት ለማስተጋባት ሞክሯል::

በቀረበው ሰነድ ውስጥ የትብብሩ ዓላማዎች ሲዘረዘሩ በተራ ቁጥር 6 ላይ እኛም እንደምናምንበት ትግሉ “... ሁሉም ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ የሚከበሩባት አዲስ፥ ፍትኃዊና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እውን እንድትሆን...” እንደሆነ ተቀምጧል:: ድርጅታችን ገና ከጥንስሱ የተለያዩ የብሔር/ብሔረሰብ እና የኅብረ-ብሔር ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶችን አቅፎ፥ ለአንዲት አዲስና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ የሚታገል ስብስብ በመሆኑ ይኸ እኛም የምንጋራውና ሙሉ በሙሉ የምናምንበት ዓላማ ነው:: ይቺ የሁላችን የሆነች አዲስ፥ ፍትኃዊና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ በሁላችንም፥ ከኛም አልፎ በመላ ኢትዮጵያውያን የጋራ ትግል የምትገነባ ናት:: ይኸ ትግል ደግሞ ኢትዮጵያውያን በፀረ-ኢሕአዴግነት ብቻ የሚሰለፉበት አይደለም:: ተጋድሎው በመላ ኢትዮጵያውያን መኻል የምንታገልላትና የምናልማት የነገዋ የጋራ አገራችን ኢትዮጵያ መልክ ዛሬ የትግግዝ፥ የወንድማማችነት፥ የጋራ እጣ ፈንታ ስሜትም እየተኰተኰቱና ከዕለት ዕለት እየዳበሩ በሚሊዮኖች ሥነ-ልቦና እንዲሰርፁም የሚደረግበት ሂደት ነው:: እነዚህ እሴቶች እንዲዳብሩና ሕዝባችን በአንድና በሙሉ ልብ እጅ ለእጅ ተያይዞ ወደ አይቀሬው ድል እንዲጓዝ ለማስቻል በኅብረታችን በኩል የስብስቡ መጠሪያ ኢትዮጵያ የሚለውን ስም በግልፅ እንዲያካትት ያቀረብነው አሳብ ተቀባይነት አላገኘም:: በዚሁም መንፈስ የትብብሩ ሰነዶች ሁሉ በቅድሚያና በዋናነት በእንግሊዝኛ ተዘጋጅተው እንዳስፈላጊነቱ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች ይዘጋጁ መባሉን ተቃውመን ሰነዶች በቅድሚያ በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ እየሠራ ባለው ብሔራዊ ቋንቋ ማለት በአማርኛ ወይም ቢያንስ በአገሪቱ ካሉት ቋንቋዎች ውስጥ በአንዱ እንዲጻፍ ከዚያ ወደ እንግሊዘኛም ሆነ ወደ ሌላ የባዕድ ቋንቋ እንዲተረጎም ያቀረብነው አሳብም ተቀባይነት አላገኘም::

በመሠረቱ አንድ የጋራ ዴሞክራሲያዊ ራእይ እስካነገብን ድረስ ይኸ ችግር በሂደት ሊፈታ የሚችል አድርገን ብናየውም ይኸንን ራእይ እውን ለማድረግ መደረግ ስላለበት ትግል ጉዳይ መሠረታዊ ብለን የተረዳናቸው ልዩነቶች በመከሰታቸው የጠነከረ የትግል አንድነት ለመገንባት እንዲቻል፥ ኢዴኃን (ኅብረቱ) የተሻለ አማራጭ ብሎ የመረጠው አካሄድ መጀመሪያ በተጠቀሱትና የፖለቲካ ልዩነቶች በተከሰቱባቸው የግንቦት እጣ ፋንታም ይሁን የዴሞክራሲያዊው ሽግግር ጉዳይ፥ የሲቪኩ ማኅበረሰብ ጥያቄም ሆነ የፖለቲካ ድርጅቶች ሚና ላይ መግባባት እንዲደረስ ግልጽ የፖለቲካ ውይይት ማካሄድና ከዚህም ተያይዞ በነዚህ ጉዳዮች ላይ አንድ መግባባት ሲደረስ ለተግባራዊነታቸው ግልፅ የሆነ ቅደም ተከተልና እቅድ ላይ ስምምነት የሚደረስበትን ሁኔታ መወያየት ሆኖ አግኝቶታል:: ስለሆነም በእነዚህ ጉዳዮች ላይ በቅድሚያ ከትብብሩ መሥራቾች ጋር ውይይት እንዲካሄድ ወስነናል::
እነዚህ መሠረታዊ ያልናቸው ልዩነቶች ምንድን ናቸው? እነዚህ ተስተካክለው የጋራ ትግሉ ፈር እንዲይዝ ኅብረታችን የሚያቀርባቸው ዋና ዋና ነጥቦች ወይም አሳቦችስ ምንድን ናቸው?

## 1. በግንቦት ድሎች ጉዳይ የተንፀባረቀው ልዩነት፤

በእኛ በኩል የተነሳው ነጥብ ይኸ የሚፈጠር ትብብር (አልያንስ) የሽግግር ዘመን ትብብር መሆኑንና ዋናው ተግባሩም በሕዝብ ትግልና መስዋዕትነት ከተገኙ በኋላ በአቶ መለስ ሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት የተነጠቁትን ድሎች ለማስመለስ ዛሬ ሕዝባችን እያካሄደ ያለውን ትግል ማስተባበርና አቅጣጫ መስጠት ነው የሚል አቋም ነበር:: ለጉባዔው ባቀረብነው ሰነድ መሠረት ዛሬ የዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ዋና ተግባር በአንድ ሂደት የግንቦትን ድሎች የማስመለስና በነሱ ላይ የመገንባት ተግባር ነው:: ይኸም ማለት በአንድ በኩል ከምርጫ በተያያዘ የታሰሩት ሁሉ እንዲፈቱ፥ ነፃው ፕረስ መልሶ በእግሩ እንዲቆም፥ ለተፈፀሙት ወንጀሎች ተጠያቂነት እንዲኖር፥ ወዘተ.... በሚሉ ጥያቄዎች ዙሪያ የሕዝቡን ትግል ማስተባበርና መምራት ማለት ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ በሕዝብ ትግል እነዚህ ድሎች ቢገኙ እንኳን የኢሕአዴግ መንግሥት ፀንቶ እስከቆመ ድረስ ተመልሰው ላለመነጠቃቸው ምንም ዋስትና ስለማይኖር ትግሉ በፀረ-ኢሕአዴግነቱ እያየለ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመሸጋገር የሚያስችሉ ሁኔታዎች እስኪመቻቹ ድረስ ሳያሰልስ መቀጠል ይኖርበታል ማለት ነው:: ኅብረቱ ልዑክ ቡድኑን ወደ ዩትሬክት ሲልክ ስብሰባው ላይ በግንቦት ድሎች ዙሪያ ማካሄድ የሚያስፈልገን የጋራ ትግል ጉዳይ ቁልፍ ቦታ ይይዛል የሚል እምነት ነበረው:: ሆኖም በስብሰባ አዘጋጅዎቹ በቀረቡት ሁለት ሰነዶች ውስጥ እነዚህን የሕዝብ ድሎች ስለማስመለሱ የጋራ ትግል ይቅርና አንድም ቦታ ስለ ግንቦት ተጋድሎና ድል የሚያወሳ ነገር የለም:: ይኸ እኛን ብቻ ሳይሆን በርካታ ዴሞክራቶችንና አገር-ወዳዶችን ስጋት ላይ የጣለ ጉዳይ ነው::

ዛሬ የግንቦት ድሎችን መከበር ጉዳይ እንደ ትግላችን አልፋና ኦሜጋ አድርገን ከሚሊዮኖች ጎን ቆመን የምንታገለው የነዚህ ድሎች መቀማት ጉዳይ ከተራ የድምፅ መስጫ ኮሮጆ ስርቆሽ አልፎ በዴሞክራሲው ሂደት ላይ የሕዝባችንን መከራ ምናልባት ለአንድ ትውልድ ሊያራዝም የሚችል መዘዘኛ የቅልበሳ ሙከራ አድርገን ስለምናየው ነው:: በዚህ የቅልበሳ ሂደት በሕዝባችን ፊት የሚጋለጡት የኢሕአዴግ መሪዎች ብቻ እንደሆኑ መቁጠር ጨርሶ የሚያዋጣ አካሄድ አይሆንም:: የአገራችን ዴሞክራቶች ሕዝባችንን ታገል፥ ተሰዋ፥ ምረጥ ብለው፥ ሕዝባችንም ታግሎ፥ ተሰውቶ በነቂስ ወጥቶ መርጦ ድልን ተጎናጽፏል:: ይኸ ድል በጠራራ ፀሐይ ሲነጠቅ ድምፅህን ለማስከበር ታገል፥ እኛም በምታደርገው ትግል ከጎንህ እንቆማለን ብለው ቃል የገቡለት ታጋይ ኃይሎች አውላላ ሜዳ ላይ ጥለውት ሲያፈገፍጉ በነሱም ቢሆን ለረጅም ጊዜ እምነት ያጣል:: ግንቦትን "መርሳት" ወይም ደግሞ ሕዝባችን ድሉን ለማስከበር የሚያካሂደውን ትግል "ምርጫው ተጭበርብሯል፥ ዓለም-አቀፍ መስፈርቶችን አያሟላም" ካሉት በኋላ በሆነ ባልሆነ ሰበብ ትግሉን ማደናቀፍና በኢሕአዴግ በኩል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መሰለፍም ለዓለም-አቀፍ ማኅበረሰቡም ተአማኒነት የሚያስገኝ አካሄድ አይደለም:: ከዚህ ሁሉ ጋር በግንቦት ሳቢያ በሕዝባችን ኅሊና የሰረጹት የሰላማዊ ለውጥ፥ የዴሞክራሲ፥ የብሔራዊ እርቅና የሕዝብ ወንድማማችነት እሴቶች በሙሉ በኢሕአዴግ መሪዎች የቂም በቀል ሸብር ገደል ገብተው ይከስማሉ:: በዚህ ኅብረተሰባችን በማንም እምነት አጥቶ አንገት በሚደፋበት ሁኔታ በቀጣዩ የ ፪ ሽህ ፪ (2002) ዓ/ም ምርጫ ደግሞ ኢሕአዴግም ስለ ነፃ ምርጫ ለመለፈፍ፥ ዓለም-አቀፍ ማኅበረሰቡም ልምጣ ልታዘብ ለማለት፥ እኛም ሕዝባችንን ተነስ፥ ታገል፥ ተሰዋ፥ ምረጥ የምንልበት ኅሊናዊ፥ የሞራልም ሆነ የፖለቲካ ብቃት አይኖረንም:: የግንቦትን ድሎች ጉዳይ እንደዋዛ መዝለሉ ወይም ደግሞ እነዚህን ድሎች ለማስመለስ የሚደረገውን ተጋድሎ የዛሬው ተልእኮ እንብርት አድርጎ ቆጥሮ አለመንቀሳቀሱ የሚያሰጋን ለዚህ ነው::

በአሁኑ ወቅት ወጣቶች፥ ተማሪዎች፥ ገበሬዎች፥ ሠራተኞች፥ ሴቶች፥ ምሁራን፥ ነጋዴዎች፥ ወዘተ... በአጭሩ በደርዘን ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች በአገሪቱና በውጭ በታሪካችን ምን ጊዜም ባልታየ ሁኔታ ከዳር እስከ ዳር ተነስተው የሕዝብ ድምፅ ይከበር ብለው እየታገሉና እየተሰው ናቸው:: ይኸ ትግል በኢሕአዴግ ሸብር ብቻ ሳይሆን እጅግ አሳሳቢ በሆነ የአመራር ክፍተት የተነሳ እየፈዘዘና ለመመዘኛ ቅልበሳ እየተመቻቸ ሲሄድ

እያየነው ነው፡፡ በመሆኑም የወቅቱ አንገብጋቢ ተግባር ይኸንን የአመራር ክፍተት ደፍኖ ሕዝባዊውን እንቅስቃሴ ከአስከፊ ቅልበሳ ማትረፍ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ አሳሳቢ ሁኔታ የማንኛውም ለጋራ ትግል በግንባር ቀደምነት ቆሜአለሁ የሚል ስብስብ ዋና ተግባር ዛሬ ለተያዘው ሕዝባዊ ተጋድሎ ግልፅ፥ ቀላልና ተጨባጭ መፈክሮች በማስጨበጥ አዲስ እምርታና አቅጣጫ የመስጠት ተግባር መሆን አለበት እንላለን፡፡ ስጋታችን የሚመነጨው ለዩትሬክት ስብሰባ ቀርበው ውይይት የተደረገባቸው ሁለት ሰነዶች ለሕዝባችን ትግል ተጨባጭ መፈክሮችም ሆነ አቅጣጫ ለመስጠት የሚችሉ ሆነው አላገኘናቸውም፡፡

በመግባቢያ ሰነዱ (ሜሞራንደሙ) ላይ የሚሠሩ መደላድሎችን ወይም መመቻቸቶችን ተግባራዊ ማድረግ ዓላማው አድርጎ የተነሳው ትብብር፤ ስለ የሕግ የበላይነት መረጋገጥ፥ ስለ ዴሞክራሲ መስፈን፥ ዴሞክራሲያዊ መሠረት ስለመጣል፥ የዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች ስለ መከበር፥ ለአካባቢው ዘለቄታዊ ሰላም፥ መረጋጋትና ብልጽግና እንዲኖር መሠረት ለመጣል በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ከባድና ውስብስብ ችግሮችንና ጉዳዮችን በወዳጅነትና በሰላም ለመፍታት በቁርጠኝነት መሰለፍ፥ ወዘተ... የሚሉ በርካታ ነጥቦች ተዘርዝረዋል፡፡ ተግባራት ተብለው ደግሞ፤ ነፃነት፥ ዘላቂ ሰላምና ዴሞክራሲ እንዲሰፍኑ የአባል ድርጅቶችንና ደጋፊዎቻቸውን ትግል ማስተባበር፥ በአካባቢው ሕዝቦች መኻል የወንድማማችነት መንፈስ እንዲሰፍን መሥራት፥ በውስጥና በአካባቢው አገሮች መኻል የሚነሱ ግጭቶችን በሰላም የመፍታት ባህልን ማዳበር፥ የዴሞክራሲ ባህልና ተቋማት ማበልጸግ፥ እህትማማች በሆኑት በኢትዮጵያና በኤርትራ መኻል በጋራ ስምምነት መሠረት መልካም ግንኙነት እንዲኖር መሥራት፥ ወዘተ.... የሚሉ ተዘርዝረዋል፡፡ በዚህ ዝርዝር ውስጥ በአቀራረብና በዚህ ስብሰባ ላይ የሚኖራቸው አስፈላጊነት ላይ፥ ከተሰብሳቢው ጥንቅር የተለያዩ አቋሞችና እምነቶች አኳያ፥ አንዳንድ አከራካሪና ያላስፈላጊ፥ ግልጽነትም የጎደላቸው፥ በተድበሰበሰ መልክ በአንደምታ ከሌሎች ተፈላጊና ከምንታገልላቸው ዓላማዎች ጋር በተጓዳኝ ተጠቅልለው የገቡ ያላስፈላጊና ተጻራሪ አስተሳሰቦች ታክለው ቀርበዋል፡፡ ያም ሆኖ በደፈናዊና እንዲሁ በሌጣውና በግልቡ ከላይ ከሚታየው ተነስቶ ኅብረቱ ልቀበላቸው ቢል እንኳ በስብሰባው ላይ ተወካዮቻችን ተከራክረው ለማስረዳት እንደሞከሩት ሁሉ፥ እነ አቶ መለስም እነዚህን ነጥቦች እንስማማባቸዋለን ከማለት አልፈው በዚህ ውስጥ የተካተቱት ዴሞክራሲያዊ እሴቶች ሁሉ በአገራችን ተረጋግጠዋል፥ እንዲጎለብቱም ጥረት እየተደረገ ነው ባዮች ናቸው፡፡ ነገር ግን ሕዝባችንና የአገራችን ዴሞክራቶች ከነዚህ ከማያታግሉ ከባድ ከባድ ዓላማዎች ወረድ ብለው "የግንቦት ድላችን የት ደረሰ?" "ተነጥቀናልና እንዴት እናስመልሳቸው?" የሚሉ ተጨባጭ ጥያቄዎች የሚያቀርቡበት ሁኔታ ውስጥ ስላለን ሰነዶቹ ተጨባጭ መልስ መስጠት የነበረባቸው ለዚህ ሕዝባዊ ጥያቄ ነበር፡፡ ፈጽሞ አልሰጡም፡፡ በዚህ እረገድ በኅብረቱና በአምስቱ ትብብር (አልያንስ) የፈጠሩ ድርጅቶች መኻል መሠረታዊ የሆኑ የአመለካከት፥ የስትራቴጂና የአካሄድ ልዩነቶች ተስተውለዋል፡፡

## 2. <u>የሁሉን-አቀፍ ጉባዔ ጉዳይ፤</u>

በኅብረቱ እምነትና እይታ ይኸ ሁሉን-አቀፍ ጉባዔ የግንቦት ድሎችን አስከብሮ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ለመሸጋገር በሚደረገው ትግል ቁልፍ ቦታ የያዘ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በትግል ላይ ላሉት ሚሊዮኖች አንዲት የትግል መፈክር ማስጨበጥ ቢኖርብን "ለሁሉን-አቀፍ ጉባዔ" የምትለው መሆን ይኖርበታል እንላለን፡፡ ይኸንን ለማድረግ ደግሞ እራሳችን ከወዲሁ ስለዚህ ጉባዔ ምንነትና ተሳታፊዎች፥ ስለሚጠበቁት ተግባራትና እንዴት፥ የትና መቸ ሊጠራ እንደሚችል ግልጥልጥ ያለና ለትግል የሚያመች አቋም መያዝ ያስፈልጋል፡፡ አሁን በዚህ ጉባዔ ሰነድ የምናየውና የሚነገረን ግን ይኸንን አያንፀባርቅም፡፡

የጉባዔው ተሳታፊዎች እነማን ናቸው? በዚህ ጉዳይ ኢዴኃኅ (ኅብረቱ) ያለውን አቋም ደግመን ደጋግመን ገልፀናል፡፡ <u>የተያዘው ትግል የምርጫ ወይም የፖለቲካ ሥልጣን</u>

ቅብብሎሽ ሳይሆን ኅብረተሰባችንን በሙሉ ከአንድ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ የአገዛዝ ሥርዓት ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማሸጋገር የሚደረግ ትግል ነው። ይኸ ደግሞ በሽግግር መንግሥትነት ወይ በሌላ መጠሪያ ተሰይሞ "የሽግግሩን ጉዳይ ለእኔ ተውት" ለሚል የፖለቲካ ድርጅት ወይም ስብስብ የሚተው ነገር አይደለም። በጠቅላላው በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚገኙ የተሰበጣጠሩ ኃይሎች የጋራ ሃላፊነት ነው። ከዚህም በመነሳት ይኸ ለሽግግሩ ቁልፍ መንደርደሪያና አስተማማኝ መሠረት መጣያ አድርገን የምናየው ጉባዔ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክና የሙያ ስብስቦች፣ የሴቶች፣ የወጣቶችና የተማሪዎች፣ የገበሬዎች፣ የሠራተኞች፣ የነጋዴዎች፣ ወዘተ... ተወካዮች፣ የሐይማኖት ተቋማት መሪዎችና የአገር ሽማግሌዎች እንዲሁም በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የሚወከሉበት ሰፊ ስብሰባ ይሆናል።

በዚህ ቁልፍ ጥያቄ ላይ የአሁኑ 'ትብብር (አልያንስ)' የሁሉን-አቀፍ ጉባዔ አስፈላጊነት ቢቀበልም በጉባዔው እነማን እንደሚሳተፉ የሚያመለክተው ነገር የለም። ሁሉን-አቀፍ ጉባዔ ሲባል በዓለም-አቀፉ ማኅበረሰብ አጋፋሪነት የፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ ከኢሕአዴግ ጋር የሚሳተፉበት ጉባዔ ለማለት ከሆነ የሽግግሩን ሂደት ጠባብ የፖለቲካ ሥልጣን መጋራት ወይም መቀባበል ሂደት አድርጎ የማየት ነገር ስለሚሆን ኅብረታችን እንደዚህ ዓይነቱን የዳግማዊ ለንደን አካሄድ ለአገራችን የሚበጅ አካሄድ ባለመሆኑ ሊስማማበት አይችልም። ለዚህ ጉባዔ በ'ትብብሩ (አልያንሱ)' በኩል የተሰጡትን ተግባራት ስንመለከት ይኸ ስጋታችን ይጨምራል።

የጉባዔው ተግባራት ምንድን ናቸው? በኢዴኃኅ ፕሮግራም ክፍል ሁለት ተዘርዝሮ በተቀመጠው መልክ የእኛ እይታ የእንዲህ ዓይነቱ ጉባዔ መሠረታዊ ተግባር የዴሞክራሲያዊ ሂደት (ዴሞክራታይዜሽን) እና የብሔራዊ እርቅ አራማጅ አካላት (ኮሚሽኖች) በማቋቋም በእነዚህ ተቋማት አማካይነት ይኸ ፀረ-ሕዝብና አፋኝ ሕገ-መንግሥት ተቀይሮ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ሽግግር የሚደረግበትን ሁኔታ የማመቻቸት አደራ ነው። በ'ትብብሩ' ሰነዶች ላይ ስለዚህ ሁሉን-አቀፍ ጉባዔ ተግባር በሚያወሳው ክፍል "አልያንሱ የሚሠራ ስምምነት ለመፍጠር አንድ ሁሉን-አቀፍ ጉባዔ እንዲጠራ ይሰራል። ይኸ ስምምነት አሁን ባለው የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ ወደ ተሟላ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መንገዱን የሚያመቻች ይሆናል" ይላል። ይኸን የኢሕአዴግ ሕገ-መንግሥት በተመለከ ኅብረታችን የጠራ አቋም ነው ያለው። ከአቀራረፅ እስከ ተግባር ላይ መዋል ጨርሶ የሕወሓት/ኢሕአዴግ ፍላጎት ማስፈጸሚያና ለአምባ-ገንን ጠባብ አገዛዙ ለዴሞክራሲያዊነት ጭምብልነት የሚገለገልበት መሣሪያ ብቻ ነው። ስለሆነም በዚህ የሕወሓት/ኢሕአዴግ ሕገ-መንግሥት ሥር ሆኖ ብሔራዊ ጥቅምን የሚያስጠብቅ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊገኝ አይችልም። ኅብረታችን በምርጫ ፺፯ ሲሳተፍ፣ ይኸ ሕገ-መንግሥት ፀረ-ዴሞክራሲና የሕዝብን ድል ለማስከበር እንደማይችል፣ መቀየርም እንዳለበትና ትግላችንም በምርጫ ዙሪያ ያሉ ሁኔታዎችን ተጠቅመን ሕዝባችንን በማደራጀት ሕጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሕዝብ የተቀበለውና የእኔ ነው የሚለው ሕገ-መንግሥት ባለቤት እንዲሆን አጋዥ ሁኔታዎችን ለመፍጠር እንደነበር በግልፅ እየነገርን እንጅ ይኸን የሕወሓት/ኢሕአዴግ አፋኝ ሕግ ተቀብሎ ለመሥራት አልነበረም። በዚህ እረገድ ኅብረቱ የተንቀሳቀሰው የሕወሓት/ኢሕአዴግ ሕገ-መንግሥት በሌላ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት እስኪተካ ድረስ ሰላማዊና ሕጋዊ ትግል ለማካሄድ በሕገ-መንግሥቱ ማእቀፍ ውስጥ የነበሩ ቀዳዳዎችን ለመጠቀም እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል። የአቶ መለስ አገዛዝ በተለይ ከምርጫው ወዲህ የሕዝብ ድምፅ ቀምቶ፣ የተከተለውን አሸባሪ ተግባር ስንመለከት ኅብረታችን ገና ከጠዋቱ በዚህ ሕገ-መንግሥት ተብየ ጉድ ሥር ሕዝባችን የሥልጣኑ ባለቤት ከመሆን እንደሚያግድና ለምን መቀየር እንዳለበት ያለንን አቋም ትክክለኛነት ነው ያረጋገጠልን።

አሁን 'ትብብሩ (አልያንሱ)' እንደወሰደው አቋም የአገራችን ችግሮች "አሁን ባለው የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ላይ የተመሠረተ..." መፍትኄ ሊያገኙ እንደማይችሉ ለእኛ

ግልፅ ነው:: በመሆኑም የዚህ ጉባዔ ዋና ተልእኮ በዚህ ሕገ-መንግሥት ላይ "ተመሥርቶ" መፍትኄ የመሻት ተልእኮ ሳይሆን ሕገ-መንግሥቱ የሚቀየርበትን ዘዴ የማመቻቸቱ ተልእኮ እንደሆነ በማያሻማ ሁኔታ ሊቀመጥ የሚገባው ነጥብ ነው:: በዚህ መልክ ከተቀመጠ ደግሞ ከፍ ብለን እንዳልነው በዴሞክራሲ አስገኝ (በዴሞክራታይዜሽን) ሂደቱ ያገባናል የሚሉ የኅብረተሰባችን ክፍሎች በሙሉ የሚሳተፉበት ጉባዔ መሆን እንደሚኖርበት ከወዲሁ በግልፅ መቀመጥ ይኖርበታል ማለት ነው:: እንደዚህ በግልፅ ከተቀመጠ ደግሞ በሰነዶቹ የተነሳው ጉባዔ የትና መቼ እንደሚደረግ በእንጥልጥል የቀረው ጥያቄ ግልፅና ለትግል የሚያመች መልስ ያገኛል ማለት ነው::

ጉባዔው እንዴት፥ መቼ፥ የት ይጠራል? የመግባቢያ ሰነዱ (ሜሞራንዱ) በዚህ ጉዳይ "የጉባዔው ቀንና ቦታ ወደፊት በ'ትብብሩ (በአልያንሱ)' አባላት ስምምነት የሚወሰን ይሆናል" ይላል:: ለአገራችን የዴሞክራሲና የሽግግር ሂደት ወሳኝ እንደመሆኑ መጠን መቼና የት ከሚሉት ጥያቄዎች በፊት ይኸ ጉባዔ "እንዴት ይጠራል?" የሚለውን ቁልፍ የቅድመ-ሁኔታ ጥያቄ በመጀመሪያ በግልፅ መመለስ ያስፈልጋል:: በእኛ እምነት ጉባዔው ምናልባት ገና ብዙ ውጣ ውረድና መስዋዕትነት በሚጠይቅ ሰላማዊ ሰልፎችን፥ የሥራ ማቆም አድማዎችንና ሌሎች የእምቢተኛነትና የአልገዛም ባይነት ተቃውሞ መግለጫ መንገዶችን (ሲቪል ዲስኦቦዲየንስ) በስልትነት እያፈራረቀ በሚጠቀም ሕዝባዊ የትግል ማዕበል የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ተሸንፎና ተገድዶ የሚጠራ ስብሰባ ነው:: ዛሬ ባለው የአቶ መለስ አምባገነናዊና አሸባሪ አገዛዝ ሥር ወይም ደግሞ በባዕዳን ኃይሎች የሆነ ሽምግልናና ግፊት የሚታሰብ እንዳልሆነ ግልፅ ነው:: ከዚህ ሃቅ ስንነሳ "መቼ ይደረጋል?" ለሚለው ጥያቄ ሊኖር የሚችለው መልስ የሕዝባችን ትግል አይሎ የሕወሓት/ኢሕአዴግን መንግሥት የሚያስገድድበት ደረጃ ላይ ሲደርስ የሚል መልስ ብቻ ነው:: "የት ይደረጋል?" ለሚለው ጥያቄ በዚያው በአገራችን ምድር ብለን እንመልሳለን:: ቦታና ቀኑ ወደፊት "በትብብሩ (በአልያንሱ) አባላት ይወሰናል" የሚለውንም አነጋገር ግድፈት የምንመለከተው ከዚህ ትንተናችን አንፃር ነው:: ወሳኙ ግን የሕዝብ ትግል ደረጃ ነው:: ይኸ የሕዝብ ትግል ደግሞ ሕወሓት/ኢሕአዴግን የሚያስገድድበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ በሌላ አነጋገር ለምንፈልገው አስተማማኝ ድል እንዲበቃ በተሳትፎውም ሆነ በአመራሩ ደረጃ የግድ "በትብብሩ (ከአልያንሱ) አባላት" ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ከፖለቲካ ድርጅቶችም የሰፋ ትግል ያስፈልጋል:: በዩትሬክቱ ስብሰባ ከተንፀባረቁት ልዩነቶች አንዱና አቅጣጫው ስጋት ያሳደረብን ጉዳይ ለዚህ ለሲቪክና ለሙያ ማኅበረሰብ የተነፈገው ትኩረት ነው::

## 3. ትግሉና የሲቪክ ማኅበራትና ስብስቦች ጉዳይ፤

ዛሬ በአገራችን እየተካሄደ ያለው ትግል ኅብረተሰባችንን ደሞክራሲያዊ ለማድረግ የሚካሄድ ትግል እንደመሆኑ መጠን የፖለቲካ ድርጅቶች ምንም እንኳን ግንባር ቀደም ሚና መጫወት ቢጠበቅባቸውም፥ ከወዲሁ ከፖለቲካ ውጭ ያሉ የተለያዩ የሲቪክና የሙያ ማኅበረሰቡ ስብስቦች በተራ ተሳትፎ፥ በድጋፍ፥ ወዘተ.... ብቻ ሳይሆን በአመራርም ደረጃ የሚሳተፉበት ሁኔታ መፈጠርና የትግል መድረኩም ሁሉን-አቀፍና ሰፊ መሆን አለበት::
በዓይናችን ሥር የሚታየውም ሃቅ የሚያመለክተው በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ በትግል ላይ ከሚገኙት ሚሊዮኖች መኻከል በወገናዊ የፖለቲካ ፕሮግራም ተካትተው የሚታገሉት ዜጎች ቁጥራቸው እጅግ አናሳ ነው:: ከነዚህ ሌላ በአገር ቤትም ሆነ በውጭ ዴሞክራሲ በአገራችን ሥር እንዲሰድ በፍጹም ቅንነትና በጎ ፈቃድ አምርረው ከልብ የሚታገሉ ተማሪዎችና ወጣቶች በሙያ፥ በጥቅም፥ በመብት፥ በብሔር ከምንም ወገናዊ የፖለቲካ ድርጅትና ፕሮግራም ውጭ ለወል አገራዊና ሕዝባዊ ዓላማ እውንነት የተደራጁ ስብስቦች፥ በትምሕርት፥ በሥራና በዕድሜ የላቀ እውቀትና ተመክሮ አካብተው፥ ይኸንን ሁሉ ለአገር ጥቅም ለማዋል የሚፈልጉ አዛውንት፥ ከግንቦት ወዲህም በፖለቲካ፥ በዲፕሎማሲ፥ በሃሳብ ይኸንኑ የዴሞክራሲ ሂደት ለማጎልበት አሁን ደግሞ ከቅልበሳ ለማትረፍ በተለያዩ ስብስቦች ተካትተው የሚንቀሳቀሱ ኃይሎችና የምሑራን ስብስቦች በርካታ ናቸው:: እነዚህ ሁሉ ሲደማመሩና ሲተጋገዙ ማንም ሊቋቋማቸው የማይችል ሕዝባዊ የትግል ማዕበል ሊፈጥሩ

እንደሚችሉ መጠራጠር አይቻልም፡፡ ይኸም በልዩ ልዩ ሙያና እውቀት የዳበረ አገር-ወዳድ የሰው ኃይል ነው የነገዋን ኢትዮጵያ ከወደቀችበት የሚያነሳት፡፡ ታዲያ ይኸ ኃይል በነገዋ ኢትዮጵያ የዳበረ እውቀቱንና ጥሪቱን ሳያመነታ እንዲያፈስና ተሳታፊም፥ አንቀሳቃሽም እንዲሆን ከወዲሁ የታገለበትና የሚያምንበት ሥርዓት ግንባታ አካል እንዲሆን ማድረጉ የተመረጠ አካሄድ ነው፡፡

በደቡብ አፍሪቃ የዘረኛው የአፓርታይድ ሥርዓት መገርሰስ የፖለቲካ ኃይሎች ብቻ አጀንዳ አልነበረም፡፡ ያ ግዙፍ አስከፊ ሥርዓት ሊገረሰስና ከዚያም በላይ ደግሞ አገሪቱ (ደቡብ አፍሪቃ) እርቅ ወደ ሰፈነበት የተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማምራት የበቃችው ፀረ-አፓርታይዱ ትግል ለፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ ሳይተው "ነገሩ ያገባኛል" የሚለው ኅብረተሰብ በሙሉ ሥፍር ቁጥር በሌላቸው ጉዳዮች ዙሪያ በፆታ፥ በሙያ፥ በሐይማኖት፥ በመብት፥ በጥቅም፥ ወዘተ... የተደራጁ ስምንት መቶ ያኽል ድርጅቶችና ስብስቦች እንዲሁም እውቅ ግለ-ሰቦች በተካተቱበት "የተባበረው ዴሞክራሲያዊ ግንባር" በተባለው ግዙፍ ስብስብ አማካይነት የትግሉ አካል ለመሆን በመቻሉ ነበር፡፡

በእኛም አገር ቢሆን የሲቪኩን ማኅበረሰብ ተሳትፎ የማያካትት ወይም ደግሞ እነዚህን የዴሞክራሲው ትግል ባለቤት የሆኑ ኃይሎች "በደጋፊነት" ሚና ወስኖ የሚካሄድ ትግል የትም የሚያደርስ አይሆንም፡፡ ከዚህ በመነሳት ኅብረታችን የተፈጠረውን 'ትብብርም (አልያንስ)' ሆነ ሌላ ወደፊት የሚመጣ የፖለቲካ ድርጅቶች ስብስብ እንደ ትግሉ አንድ አካል እንጅ እንደ ዋና መአከል አድርጎ አይመለከተውም፡፡ በመሆኑም ነገ የሕወሓት/ኢሕአዴግ በሕዝብ ትግል ተገድዶ በአገራችን ለሚደረገው ሁሉን-አቀፍ ጉባዔ ዛሬ ሁሉን-አቀፍ ትግል እንደሚያስፈልግ አጥብቀን እናምናለን፡፡ ከዚህም በመነሳት በውጭ አገር በአስቸኳይ የአቶ መለስን ሽብርተኛ አምባ-ገነን አገዛዝ የሚቃወሙና ለሕዝባችን መልካም ሥርዓት ግንባታ የሚታገሉ ኃይሎች ሁሉ የሚሳተፉበት ሁሉን-አቀፍ ጉባዔ ተጠርቶ አንድ ሁሉን-አቀፍ የጋራ አካል እንዲፈጠር ኅብረታችን ሃሳብ አቅርቧል፡፡ ይኸ ኢዴኃኅ (ኅብረቱ) እንደ ቁልፍ ጥያቄ አድርጎ የወሰደው ጉዳይ 'በትብብሩ (አልያንሱ)' ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ኅብረቱ እነሆ አሁንም ይኸ እንዲሆን ጥያቄውንም ጥሪውንም በድጋሚ ያቀርባል፡፡

## 4. ቀጣዩን ሂደት በተመለከተ ያለን አሳብ፤

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት አባል ድርጅቶች በነዚህ ሁሉና በሌሎች በርካታ የትግል ስትራቴጂ ልዩነቶች የተነሳ የኅብረቱ ልዑካን ቡድን በዩትሬክት ስብሰባ የወሰደውን አቋም በመደገፍ፤

አንደኛ፡- በእኛ እይታ 'ትብብሩ (አልያንሱ)' አገራችን ወደ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ለማሸጋገር በሚደረገው ትግል የተባበረ ተሳትፎ ለማድረግ የሚጥር የሽግግር ወቅት ትብብር መሆን ስለሚኖርበትና በዚህ ትግል ውስጥ ዋናው የሕዝባችን አጀንዳ የግንቦትን ድሎች አስመልሶ በነሱ ላይ የመገንባት አጀንዳ ስለሆነ ይኸንን የ'ትብብሩ (የአልያንሱ)' ሰነዶች እረስተው ያለፉትን ጉዳይ አስመልክቶ የጋራ ግንዛቤ ስለሚያዝበትና ይኸንን ሕዝባዊ አጀንዳ እውን ለማድረግ ተጨባጭ የድርጊት ፕሮግራም ስለሚነደፍበት ሁኔታ ከስብስቡ መሥራቾች ጋር ውይይት እንዲደረግ፤

ሁለተኛ፡- የባዕዳን ኃያላንም ይሁኑ ሌሎች ኃይሎች በሚያደርጉት ቀጥተኛም ይሁን ተዘዋዋሪ ጫና፥ ግፊትና ተጽዕኖ ነገሮችን በጠባብ መልክ የማየትና እንደ ስመ-ጥፉው የ፲፱፻፹፫ ዓ/ም (1991) የለንደን ጉባዔ አሁንም "ዋና ዋና" በሚባሉ ጥቂት የፖለቲካ ኃይሎች ድርድር ተብየ ዝግ ዱለታ-ቀመስ አካሄድ የአገራችንን ችግሮች ለመፍታት የሚደረግ አዝማሚያ የሕዝባችንን ትግል ከፋፍሎ ለኢሕአዴግ አገዛዝ የቅልበሳ ሂደት ሁኔታዎችን የሚያመቻች በመሆኑ፥ የአገራችንን ዴሞክራቶች በሙሉ ስጋት ውስጥ እየጣለ በመሄድ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ የባዕዳን ግፊትና ጫና ይልቅ ማዳመጥ ያለብን የሕዝባችንን የልብ ትርታና ግፊት መሆን ይኖርበታል፡፡

ይኸ ማለት፤

ሀ)- ማንኛውም ከሕወሓት/ኢሕአዴግ ጋር የሚደረግ ድርድር ከፖለቲካ ድርጅቶችና ከሲቪክ ማኅበራት መሪዎችና ታጋዮች ጀምሮ በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ወጣቶች፥ ተማሪዎች፥ ገበሬዎች፥ ወዘተ.. ከየታጎሩበት አስር ያለ አንዳች ቅድመ-ሁኔታ ሳይፈቱ እንዳይደረግ፤

ለ)- የዚህ ድርድር ዋና አጀንዳ ከፍ ብለን ባብራራነው መልክ ሁሉን-አቀፍ የሽግግር ጉባዔ በአገራችን ምድር የሚደረግበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንዲሆን፤

ሐ)- ይኸ ድርድር ከፖለቲካ ኃይሎች ጋር ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል በጠቀስነው መሠረት በውጭ ከሚደረግ የተቃዋሚው ክፍል ሁሉን-አቀፍ ጉባዔ ከሚፈልቅ ሁሉን-አቀፍ አመራር ጋር ስለሚሆንበት ዘዴ ከ'ትብብሩ (አልያንሱ)' መሥራቾች ጋር ውይይት እንዲደረግ፤

<u>ሦስተኛ፡-</u> ይኸ አካሄድ በተጨባጭ እውን ሊሆን የሚችለው ትግሉ አይሎ የሕወሓት/ኢሕአዴግን መንግሥት ለኅብረተሰቡ ጥያቄዎች አዎንታዊ መልስ እንዲሰጥ የሚያስገድድበት ደረጃ ላይ ሲደርስ ብቻ ነው። በመሆኑም የታሰሩት መሪዎችና ሌሎች ንፁኃን ዜጎች ሁሉ እንዲፈቱና ለተፈጸመው ግፍ ሁሉ ሥርዓት ያለውና ሕጋዊ ተጠያቂነት እንዲኖር ብቻ ሳይሆን ከዚያም አልፎ ትግላችንንና የጋራ ድላችንን በሁሉን-አቀፍ የሽግግር ጉባዔ ለመቋጠር እንዲቻል በነዚህ ግልፅ መፈክሮች ዙሪያ ሕዝባችን በተቀናበረ መልክ በሰላማዊ ሰልፎች፥ በሥራ ማቆም አድማዎችና በሌሎች ሰላማዊ የተቃውሞ መግለጫ ስልቶች፥ መንገዶችና ዘዴዎች ተንቀሳቅሶ ትግሉ አዲስ እመርታ እንዲያገኝ ስለምንከተለው ስትራቴጅና መተላለፍ ስለሚገባቸው ሃላፊነት የተላበሱ የጋራ ጥሪዎች ውይይት እንዲደረግ፡

አራተኛ፡- ይኸንን በውጭም በውስጥም የሚደረግ የተቀናበረ የሕዝብ ትግል ለማስተባበር እንዲቻል ዝርዝርና ተጨባጭ መርኃ-ግብር ለመንደፍና ለዚህም ተግባራዊነት ከፖለቲካ ድርጅቶች የሰፋ የጋራ አመራር አካል ስለሚያስፈልግ በውጭ አገር አንድ ሁሉን-አቀፍ ጉባዔ በአስቸኳይ ስለሚጠራበትና ለዚህም አዘጋጅ የተግባር አካል (ኮሚሽን) ስለሚቋቋምበት ዘዴ ውይይት እንዲካሄድ ለኅብረቱ ማዕከላዊ ሥራ አመራር ኮሚቴ መመሪያና ሃላፊነት ሰጥቷል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የተቃዋሚው ኃይሎች ትግላቸውን እንዲያስተባብሩና የመከራው ጊዜ እንዲያጥር ፍላጎቱ ነውና፥ ማንኛውም ትብብር የሕዝብን መስዋዕትነት የሚመጥን፥ ሕዝባችን ያጣውንና የተቀማውን የሚያስመልስ እንጅ በግንቦት ወደሻራቸው መከፋፈልና የድርጅቶች የሥልጣን ቅብብሎሽ ወይም የአፈናና የጭቆና አዙሪት መቀጠል እንዳይሆን በቅንነት፥ በግልጽነትና ትልቁን የአገርንና የሕዝብን መብትና ክብር ባከበረ መልኩ መሆን እንደሚኖርበት ኅብረቱ ያለውን እምነትና የሚጠበቅበትንም ድርሻ በሃላፊነትና በወገናዊ ስሜት እንደሚወጣ ያለውን ቁርጠኛ አቋም ሲገልጽ በአክብሮት ነው።

ለአስተማስማኝ የሕዝብ ድል የጋራ ትግል!!
የኢትዮጵያ ሕዝብ በጋራ ሁሉን-አቀፍ ትግሉ የተቀሙ ድሎቹን ያስመልሳል!!!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
ግንቦት ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington, D.C. 20056-3246,U.S.A
ስልክ/Tel.: 202-291-4217;
ፋክስ/Fax: 202-291-7645

ኢትዮጵያ (Ethiopia)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box
Addis Abeba,Ethiopia
ስልክ/(Tel.) 251_______
ፋክስ/Fax:2511________

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague,
Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132